በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# መጽሐፈ ነህምያ - ክፍል ፬


## መምህር፦ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:-** kesisolomon4@gmail.com


To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

***ቦታ፦*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ጥቅምት ፯ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም.**

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፬

- ዛሬ መጽሐፈ ነህምያን ከመሪነት አንጻር ማጥናት የጀመርንበትን ትምህርት አራተኛ ክፍል እንመለከታለን። ይልቁኑ በዓለም፣ በቤተ ክርስቲያንም ሳይቀር ከፍተኛ የመሪዎች እጥረት ባለበት በዚህ ዘመን እግዚአብሔር ክርስቲያኖች ሁሉ ለመሪነት እንዲበቁ የመሪነት ችሎታ እንዲያዳብሩ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የሚመሩ እንዲሆኑ ይሻል። እግዚአብሔር ሁላችንም የመሪነትን ስጦታና ብቃት እንዲሰጠን ፈቃዱ ይሁንልን።
- ማንኛውም መሪ ከወቀሳ ወይም ከትችት የነጻ አይደለም። እግዚአብሔር ለመሪነት የመረጠን ከሆንን ወቀሳን ወይም ትችትን ለመቀበል መዘጋጀት አለብን። ትምህርት የምንወስድበት በትህትናና በየዋህነት የምንቀበለው ነቀፋ አለ፤ እንዲሁም ለማዳከም የሚመጣ ገንቢ ያልሆነ ተራ ነቀፋ ወይም ትችት ደግሞ አለ፡- ይህንንም ከውስጣችንም ሆነ ካጠገባችን ፈጽመን በማራቅ የጀመርነውን ሥራችንንና ጉዞአችንን መቀጠል ይጠበቅብናል።
- ስለዚህ ትምህርት የምንወስድበትና እርምት የምናደርግበት ነቀፋ አለ፤ እንዲሁም የምንተወው ወይም እንዳይጎዳን የምንጠነቀቅበት ነቀፋ ወይም ወቀሳም አለ።
- ወደ ነቀፋው ከማለፋችን በፊት በአዲስ ኪዳን ታላቅ ምሳሌ የምናደርገው ቅዱስ ጳውሎስ ራሱን አስመልክቶ ስለ መሪነትና ስለ አገልግሎት የጻፈልንን እንመለከታለን። ‹‹ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን።›› ***ካል ቆሮ 2:7።***
- ይህ የእኛ የሆነው ወንጌል መዝገብ ነው፤ ይህም መዝገብ በሰውነታችን (በሸክላ ዕቃ) ውስጥ የተቀበረ ነው። ይህ የሸክላ ዕቃ ያንጠባጥባል (ያፈሳል)፣ የሚያስተማምን አይደለም፣ ስስ ነው። ቢሆንም እግዚአብሔር ግን መዝግብን በውስጡ አኖረው። ይህም የሚያረጋግጥልን እግዚአብሔር እንዲሁ በሆነ ተራ ኑሮው በሰው ዘንድ በተረሳ ሰው እንኳ ሳይቀር እንደሚጠቀም ለታላቅ መሪነትም እንደሚያበቃው ክብሩን እንደሚገልጥበትና ክብሩም የእርሱ የእግዚአብሔር እንደሆነ ነው።

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፬

- ቅዱስ ጳውሎስ የነገረን እግዚአብሔር እናንተን፣ እኔንም ሆነ ማናችንንም ቢሆን ሰባራ ሸክላ መሆናችንን እስካመንና እስከተራመድን ድረስ መዝገቡን በውስጣችን ያኖራል በማለት ነው፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ በመቀጠል ‹‹በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም፤ እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም፤ እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም፤ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም፤ የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን። የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሚሞት ሥጋችን ይገለጥ ዘንድ እኛ ሕያዋን የሆንን ከኢየሱስ የተነሣ ዘወትር ለሞት አልፈን እንሰጣለንና። ስለዚህ ሞቱ በእኛ ሕይወቱም በእናንተ ይሠራል።›› ***2ኛ ቆሮ 4፡8፡፡*** በማለት መሪ ዘወትር የክርስቶስን መከራ እንደሚሸከም፣ የክርስቶስም ሕይወት እንደሚታይበት ነገሮናል፡፡ ይህም ማለት የምንሰጠው አገልግሎት ለሕዝቡ የምናቀርብለት የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌነት እንጂ የተለየ ስጦታ እንዳልሆነ የሚያስታውሰን ነው፡፡
- ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም›› እንዳለ ማንኛውም የእግዚአብሔርን ሥራ ሊሠራ ሆነ ሊያገለግል የሚወድ ሁሉ የግድ በዚህ ውስጥ ማለፍ አለበት፡፡
- ጌታችን ‹‹ሳምራዊ፣ ብዔል ዜቡል፣ እብድ፣ አሳች፣ ወዘተ›› እየተባለ ምን ያህል ጊዜ ተነቀፈ? ከኃጢአተኞች ጋር መብላት ይወዳል፣ ሕግን ትሽራለህ፣ … እየተባለ በሁሉ ተነቅፏል ተሰድቧልም፡፡
- ከቅዱስ ጳውሎስና ከነህምያም የምንማረው እግዚአብሔርን ሊያገለግል የመረጠ፣ እግዚአብሔር እንዲጠቀምበት የወደደ፣ መሪ ሊሆን የሚሻ ማንኛውም ሰው በመነቀፍና በመሰደብ ውስጥ ማለፍ እንዳለበት ነው፡፡ ታዲያ እኛ ስስ ነን? ወይስ ይህን ለመቀበል የተዘጋጀን ነን? ከጌታው የሚበልጥ ባሪያ የለም፡፡ እሱን ወቅሰውት ሰድበውት ከሆነ እኛንም የግድ ይሰድቡናል፣ ሊሰድቡን ሊወቅሱሰንም ይገባል፡፡
- እግዚአብሔር እንደ ነህምያና ቅዱስ ጳውሎስ ያሉ ደካሞችን ደካማነታቸውን ሳይቀር ክብሩን ለመግለጥ ተጠቅሞበታል፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፩

- እግዚአብሔር ነህምያን የኢየሩሳሌም ቅጥሮች እንዲሠራ መምረጡ ጉዳዩን መንፈሳዊ ላያስመስለው ይችላል፤ ሥራው በኢየሩሳሌም ዙሪያ ግንብ መገንባት ነውና፡፡ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለነህምያ ለሕይወት ዘመኑ ያቀደለት እቅድ ይህ ነበር፡፡ እርሱም ይህን ሠራ፡፡ ማንኛውም ሰው ያላሳየውን የመሪነት ብቃት አሳየ፡፡ ነህምያም ለመሪነት ሕይወት ምሳሌያችን፣ አብነታችን (ሞዴላችን) ነው፡፡
- በመጽሐፈ ነህምያ ምዕራፍ ሦስትና አራት ላይ ነህምያ በነቀፋ እንኳ ሳይንበረከክ እንዴት ሥራውን እንደሠራና ኃላፊነቱን እንደተወጣ እንማራለን፡፡
- በምዕራፍ ሦስት እንደምናነበው ሕዝቡን ሰበሰበ፣ ሥራውን አደራጀ፣ የምትኖሩት በዚህ አቅራቢያ ከሆነ ይህን ገንቡ (ቅጥሩን ሥሩ)… እያለ ሥራውን አከፋፈለ ኃላፊነትን ሰጠ፡፡ (Distribution & Deligation of the job)
- ‹‹ታላቁም ካህን ኤልያሴብ ወንድሞቹም ካህናት ተነሥተው የበግ በር ሠሩ ቀደሱትም፥ ሳንቃዎቹንም አቆሙ እስከ ሃሜአ ግንብና እስከ ሐናንኤል ግንብ ድረስ ቀደሱት።…›› ***<u>ነህ 3፡1-ፍም፡፡</u>*** እንዳለ ከቤታቸው ባጠገብ ያለውን እገሌና ቤተሰቡ ሠሩት እያለ ምዕራፉ ይቀጥላል፡፡ እያንዳንዱም ቅጥሩን (ግንቡን) ገነባ፡፡
- የጀመሩትም ሊቀ ካህኑና ካህኑ - መሪዎች ናቸው፡፡ ቆሞ በመስበክ ምትክ ተነስተው የድንጋዩን መስበሪያ (መጥረቢያ) መስደው ሠሩ፤ ይህም ታላቅ ምሳሌነት ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ቅጥሩን የሰሩትን የሰዎችን ስም ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ስም መጠቀስ ስለምን አስፈለገ? እግዚአብሔርን እነዚህን የእቅዱና የቅጥሩ ሥራ ላይ የተሳተፉትን ማክበር ስለፈለገ (ስለወደደ) ነው፡፡ ይህም እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያከብርበት መንገዱ ነው፡፡ አንድ ነገር እንገነባለን ስማችን ለመታሰቢያነት በዚያ ይደረጋል፡፡
- እግዚአብሔርም በዓለሙ የሚፈርደው እንደ እምነቱ፣ ሥራው፣ ወዘተ ነው፡፡ በሕይወት መጽሐፍም ቅጥሩን የሠሩ ሰዎች ስም ተጽፏል፡፡ እያንዳንዳችን ከስማችን ቀጥሎ የሚጻፈው ምን ይሆን? ራሳችንን እንጠይቅ እንጸልይበትም፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፬

- ሥራው ሲጀመር፣ የቅጥሩም ግንባታ በከተማዋ በኢየሩሳሌም ዙሪያ ከፍ ማለት ሲጀምር፣ የተለያዩ የሥራ እንቅስቃሴዎች በከተማዋ ዙሪያ በስፋት ሲታዩ ሕዝቡ ደስ ሊሰኝ ይገባዋል፤ ይህ ግን ለሁሉ አይደለም ተቃዋሚዎች፣ ወይም ዲያቢሎስ በዚህ አይደሰቱም።
- የእግዚአብሔርን ሥራ ሠርተን ዲያቢሎስ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ስለ ሥራችን እንዲያጨበጭብልን መጠበቅ የለብንም። ለእግዚአብሔር መንግሥት አንድ ነገር ሠርተን ዲያቢሎስ የማይቃወመን ከሆነ አንድ ችግር አለ ማለት ነው፤ ምናልባትም ሥራውን ከዲያቢሎስ ጋር አብረን እየሠራነውም ሊሆን ይችላል። ታላቁን የእግዚአብሔርን ሥራ የምንሠራ ከሆን የግድ ከዲያቢሎስ ተቃውሞ ሊኖርብን እንደሚገባ ፈጽመን አንዘንጋ።
- በማንኛውም ድርጅትም ውስጥ የበጎ ነገር ተቃራኒ ወይም ተቃዋሚ የሆኑ፣ ለውጥን የሚጠሉ፣ በለውጥ ወይም በእድገት የሚጎዱ ሰዎች አሉ። ምክንያቱም እድገት፣ ለውጥ፣ ስኬት አልፎአቸው ይሄዳል ከቁጥር የማይገቡ ትኩረት የማይሰጣቸው ሰዎች ያደርጋቸዋልና።
- አንድ ለየት ያለ ታላቅ ነገር ስንሠራ አንዳንድ ጥሩ የሚባሉ ሰዎች ሳይቀሩ ሥራችንን ሳይወዱት ቀርተው ይቃወሙናል። ብዙ ጊዜ መልካም ነገር ስንሠራ ተቃውመውን ቆይተው ሥራችን የእግዚአብሔር ሥራ ነውና እንዲህ ያለ ሥራ መቸም አልተሠራም ብለው ሲያደንቁ ሊገኙ ይችላሉ።
- እንዲህ ያሉ ሰዎች መልካሙ ሥራ ምንም ያህል መልካም ቢሆን እንዳንሠራው ሊቃወሙን ይችላሉ። እነዚህን እንዲህ ያሉ ነቃፊዎችንም ፈጽመን መስማት አይገባንም።
- በጎ ሥራን መጥፎ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ አንዳንድ በጎ የሚባሉ ሰዎች ሳይቀሩ ይቃወማሉ፣ ዲያቢሎስም መልካምና መጥፎ ሰዎችን በአንድ ላይ በማሰለፍ ሳይቀር  መልካም ሥራን ይቃወማል።

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፬

- ሥራውን ለመቃወም ወላጆቻችንን፣ የቅርብ ሰዎችን... ሊጠቀም ይችላል፡፡ ይህንም መርምሮ ሊረዳውና ሊያውቀው የሚችለው መንፈሳዊ ሰውና መሪ ነው፡፡ የተቃውሞው መንሥኤ ምንድር ነው? ተቃዋሚው ማነው? ለምን ይቃወማል? ይህ ተቃውሞ ከማን ነው? እያለ ይጠይቃልና፡፡ ***ቀዳ ቆሮ 2፡13-15፡፡***
- አንድ ታላቅ ሥራ ስንሠራ ዲያቢሎስ ቀርቦ በደካማ ገናችን በኩል በመምጣት በጥብቅ እንደሚጋፋን እንወቅበት እንጂ ‹‹አቤት እንዴት ያለ ድንቅ ነገር እየሰራህ ነው እግዚአብሔር ይባርክህ፣ አሁን ጥቂት እረፍት እሠጥሃለሁ›› እንዲለን መጠበቅ የለብንም፡፡
- ‹‹ሰንባላጥም ቅጥሩን እንደ ሠራን በሰማ ጊዜ እጅግ ተቈጣ፥ ተበሳጨም፥ በአይሁድም አላገጠ።›› ***ነህ 4፡1፡፡*** ሰንባላጥ አይሁዳዊ፣ በኢየሩሳሌም የራሱ ሥራ ያለው፣ የኢየሩሳሌም ደካማነትዋ ቀጣይ እንዲሆን የሚሻ ሰው ነው፡፡
- ሰንባላጥ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች ስለ ሚሠሩት ሰዎች በሰማ ጊዜ እጅግ ተቆጣ፡፡
- እስኪ አሁን ምላሽ የማትሰጡበትን ጥያቄ ልጠይቃችሁ? ተስፋ የመቁረጣችሁ ልክና መጠን እስከምን ድረስ ነው? ሲናገሩን በቃል ብቻ የምንሳነፍ (ተስፋ የምንቆርጥ) ነን?
- አንድ ቤታችንን ለመሥራት በምንፈልግበት ወይም ከከተማ ወደ ገጠር ሄደን በምንፈጽመው ነገር ዕቅድ ቢኖረንና ሰዎች ምን ሆነሃል/ነክቶሃል ብለው ጉዳዩን ቢያጣጥሉብን በንግግራቸው ብቻ እንሳነፋለን?
- ወይስ ተቃውሞ ወይም ነገሩ እንዳይሆን በሚያከላክሉ የተነሳ (ይህን ካደረግኸው ባልንጀራዬ አይደለህም (አልደግፍህም)፣ እቃወምሃለሁ፣ እጎዳሃለሁ ቢሉን የጀመርነውን ከማከናወን እንሳነፋለን?
- ወይም የሚያሳንፈን ወይም ወደ ኋላ የሚመልሰን የሚደርስብን አካላዊ ጉዳት ነው? ወይስ ውድቀት ወደ ኋላ ይመልሰናል? በአጠቃላይ የቃላት ውርወራ፣ ተቃውሞ ፣ አካላዊ ቅጣት፣ ውድቀት አራቱ አሳንፈውን ወደ ኋላ ይመልሱን ይሆን? ወይስ መልሰን ለመሥራትና የተበላሸውን ለማስተካከል የምንጣጣር ነን?

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፬

- ይህ ጉዳይ ጥቂት ማሰብ የሚፈልግ ነው፡፡ ቃላት የሚያሳንፉን ከሆን በትልቅ አደጋ ውስጥ መሆናችንን ያመላክታሉ፡፡ ያም ሆኖ ልንቀጥል እንችላለን፡፡
- አሁን ሰንባላጥ ‹‹ በወንድሞቹና በሰማርያ ሠራዊትም ፊት። እነዚህ ደካሞች አይሁድ የሚሠሩት ምንድር ነው? ይተዉላቸዋልን? ይሠዋሉን? በአንድ ቀንስ ይጨርሳሉን? የተቃጠለውንስ ድንጋይ ከፍርስራሹ መልሰው ያድኑታልን? ብሎ ተናገረ። አሞናዊውም ጦብያ በአጠገቡ ቆሞ። በድንጋይ በሚሠሩት ቅጥራቸው ላይ ቀበሮ ቢመጣበት ያፈርሰዋል አለ።›› ***ነህ 4፡2፡-3፡*** እንደተባለ አላገጡባቸው፣ አፌዙባቸው፡፡ ማንኛውም መሪ ወደ ኋላ የሚመልሱትን ነገሮች ልክ ወይም መጠን የግድ ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡
- ይህን የተናገረው ማነው? ከጀርባው ያለው ድብቅ አጀንዳ ምንድን ነው? ይህን የሚናገረው የሚያስብላቸውና የሚጠነቀቅላቸው ሰው ነው ወይስ ዝም ብሎ በሥጋዊ ቅንዓት የተቃጠለ ሰው? ምንጩን ለይተን መስማት አሊያም ዝም ማለት ይጠበቅብናል፡፡
- እነዚህ ሰዎች የተቃወሙት በእግዚአብሔር የታቀደውን፣ የተሰናዳውን፣ የተገነባውን የእግዚአብሔር ሥራ ነው፡፡ መቶ ፐርሰንት ሥራው የእግዚአብሔር ቢሆንም ሰዎች ሁሉ ይደግፉታል ብለን ማሰብ የለብንም፡፡
- ልጆችን በጥበብና በሞገስ ማሳደግ የእግዚአብሔር ሥራ ነው፡፡ ይህን የሚሠሩ የእግዚአብሔርን ሥራ ይሠራሉ፤ ልጆች የእግዚአብሔር ግንቦች ናቸው፣ እየተገነቡ ማደግ አለባቸው፤ ቢሆንም ተቃውሞ አለው፡፡
- ተልዕኮአችን በእግዚአብሔር ከታቀደ፣ ከተሰናዳ፣ ከተከናወነ ተልዕኮው የእኛ ወይስ የእግዚአብሔር ተልዕኮ ነው? አዎ የእግዚአብሔር ነው፡፡ እንዲህ ያለውን ሥራ የሚነቅፉት የሚሠራውን ሰው ሳይሆን በትክክልም የሚነቅፉት ቅዱስ ጳውሎስና ቅዱስ ያዕቆብ እንደጻፉት ይህን ሥራ ይሠሩ ዘንድ ሰዎችን ያዘጋጀውን እግዚአብሔርን ነው፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፬

- **ነህምያም** ‹‹አምላካችን ሆይ፥ ተንቀናልና ስማ ስድባቸውን በራሳቸው ላይ መልስባቸው በምርኮ አገር ለብዝበዛ አሳልፈህ ስጣቸው። በደላቸውንም አትክደን፥ ኃጢአታቸውም ከፊትህ አይደምሰስ በሠራተኞች ፊት አስቆጥተውሃልና።›› ***ነህ 4፡4፡-5*** ፡፡
- ፈጽመህ ይቅር አትበላቸው አለ መልካም ጸሎት ነውን? ነህምያ እዚህ ላይ ሁለት ሥራዎች ሠርቷል፡፡ አንደኛ ጸለየ ከዚያም ሥራውን ቀጠለ፡፡ ለምንጸልየው ጸሎት ነቀፋን ለመቀበል እንዘጋጅ፡፡
- ጠንካራ ስብእና ያላቸው ሰዎች ይጀምራሉ፣ ይጸልያሉ ለተፈጸመባቸውም ጥቃት ምላሽ ይሰጣሉ፣ ጠላቴ ሆይ አገኘሁህ ይላሉ፤ እነዚህ ሰዎች እግረ መንገዱንም ደካማ ጎንም ይገኝባቸዋል፡፡
- አንድ ምሳሌ እንመልከት፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ አንዱ አገልጋዩ ቅዱስ ማርቆስ ነበር፡፡ ቅዱስ ማርቆስ የመጨራሻውን ጉዞ ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር አልተጓዘም ነበር፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም ፈጽሞ ከኛ ጋር አይመጣም ብሎ ከበርናባስ ጋር መለያየት ሆነባቸው፡፡ ለምን? በሕይወቱ መጨረሻ ለጢሞቴዎስ በላከለት መልእክቱ ማርቆስን አምጣልን በአገልግሎታችን እጅግ የሚጠቅመን ነውና ብሏል፡፡ ባለፈው አብሮን አልሄደም፣ የአውሮፕላን ቲኬት አልተቆረጠለትም፣ በሚሄዱት ዝርዝር ውስጥ የለም፣… ብሎ ተቆጣ፡፡ በርናባስም… ማርቆስም እኔም የለንም አለው፡፡ ይህም ማለት ምላሽ በመስጠት እንፈተናለን ለማለት ነው፡፡ ***ሥራ 15፡፡***
- ነህምያ ምላሽ አልሰጣቸውም፡፡ ከፋርስ ያመጣቸው ወታደሮች አብረውት ነበሩ ሊጎዳቸው ይችል ነበር፡፡ በመንፈሳዊ መንገድ በጸሎቱ መለሰላቸው፣ በልቡ መለሰላቸው - የተሰማውን ተናገረ፡፡ አዎ እኛም እንዲሁ እንደ ነህምያ በእግዚአብሔር ፊት በውስጣችን የተሰማንን እንናገር፡፡ ነገር ግን የተናገርነውን እግዚአብሔር ያደርገዋል ብለን አንደምድም፡፡
- እኛም እንደ ነህምያ ስጋታችንን፣ መሰደባችንን፣ ቁጭታችንን፣ … ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እናቅርበው…. እናፍሰው፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፬

- ‹‹ቅጥሩንም ሠራን ቅጥሩም ሁሉ እስከ እኵሌታው ድረስ ተጋጠመ የሕዝቡም ልብ ለሥራው ጨከነ።›› ***ነህ 4፡6፡፡*** እንደተባለ ነህምያ ነቀፋውን ተቀብሎ ሥራውን ስለቀጠለ ዲያቢሎስ አልተወውም፡፡
- ‹‹ሰንባላጥና ጦብያም ዓረባውያንም አሞናውያንም አሽዶዳውያንም የኢየሩሳሌም ቅጥር እየታደሰ እንደ ሄደ፥ የፈረሰውም ሊጠገን እንደ ተጀመረ በሰሙ ጊዜ እጅግ ተቈጡ። መጥተውም ኢየሩሳሌምን ይወጉና ያሸብሩ ዘንድ ሁሉም በአንድነት ተማማሉ።›› ***ነህ 4፡7-8፡፡*** እንደተባለ ሥራውን ሲቀጥል ተቃውሞ አስነሱ፡፡ ጠላቶች በሙሉ ተሰበሰቡ፡፡ መሰብሰባቸውም የቅጥሩን ሥራ ለማጓተት ብቻ አልነበረም ሥራውንም ለማቆም ነበር እንጂ፡፡
- ነህምያ ምን አደረገ? ‹‹ወደ አምላካችንም ጸለይን፥ ከእነርሱም የተነሣ በአንጻራቸው ተጠባባቂዎች በሌሊትና በቀን አደረግን።›› ነህ ***4፡9፡፡*** እንዳለ ወደ አምላኩ ጸለየ ጠባቂዎችን በሌሊትና በቀን አደረገ፡፡
- ጸለየ፣ ጠባቂዎችን አደረገ፣ በጥንቃቄ ተራመደ፡፡ ለነገሮችም ሁሉ ዝግጁ መሆኑን ገለጠ፡፡
- እስካሁን ነህምያና ሕዝቡ በርትተው የቃል ጦርነቱን ተቋቁመው የቅጥሩን ሥራ መቀጠላቸውን አይተናል፡፡
- ተቃውሞው ግን ቀጥሏል፣ መልኩና ቅርጹም በተጠናከረ መልኩ በነህምያ ላይ እያደገ ሄዷል፡፡
- ይህም የእግዚአብሔርን ሥራ ስንሠራ የሚገጥመን ችግር ነው፡፡ ይህም ዓይነት ፈተና ሁላችንንም ይገጥመናል፡፡ በርካታ ሥራዎችን እንጀምራለን አንፈጽምም፤ በቀላሉ ወደ ኋላ እንመለሳለን፡፡
- ዛሬ ብዙ የሚያበረታቱን ነገሮችን በዙሪያችን አናይም፤ በርካታዎቹ ነገሮች ተስፋ የሚያስቆርጡ ወደ ኋላም የሚመልሱ ናቸው፡፡ ዲያቢሎስ ማብሪያና ማጥፊያችንን ጥጋችንን ያውቃል፡፡ በቃላት ውርወራ፣ በተቃውሞ፣ በአካላዊ ጉዳት፣ ወይም በመውደቃችን ተስፋ የምንቆርጥ ነን? ልካችን እስከ ቃላት ውርወራ ከሆነ እዚያ ጫፍ ድረስ ወስዶ ይዋጋናል፣ ከዚያ አልፈን በተቃውሞ ከተቸገርን እስከዚያች አድርሶ ናዳውን ያወርድብናል፡፡ ስለዚህ ጫፋችንን ወይም የመፈተኛ ጥጋችንን አውቀን ተስፋ ባለመቁረጥ እንቀጥል፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፬

- ኢዮብ ልጆቹ ሞቱ፣ … ታገሠ መከራው ሲረዝም ግን ተመረረ። እኛ ገደባችንን ጥጋችንን እናውቀዋለን? ዲያቢሎስ የእግዚአብሔር ሥራ ስንሠራ ጥጋችንን ስለሚያውቅ እስኪያደርሰን ድረስ ይታገለናል ይፈትነናል። *መጽ ኢዮ 1-42።*
- በዛሬው ትምህርታችን የምንወስደው ጭብጥ ያለ ቃላት ጦርነት (ነቀፋና) ተቃውሞ ማንንም እንደማንመራ ማወቅና ይህም ሲገጥመን በጸሎት በእግዚአብሔር ዘንድ እንጂ በሰው ዘንድ ማሰማት እንደሌለብን ነው።
- ጸሎት ብቻ ሳይሆን ጠባቂዎችን ማድረግ ካለብን እናድናደርግ፣ እግዚአብሔር በሰጠን አእምሮ ተጠቅመን መፍትሔ እንድንሰጥ እንደሚጠበቅብንም እንማራለን።
- ሳምንት እንደፈቃዱ *ነህ 4፡10-23።* እንመለከታለን ‹‹ይሁዳም። የተሸካሚዎች ኃይል ደከመ፥ ፍርስራሹም ብዙ ነው ቅጥሩንም እንሠራ ዘንድ አንችልም አሉ። ጠላቶቻችንም። ወደ መካከላቸው እስክንመጣና እስክንገድላቸው ድረስ ሥራቸውንም እስክናስተጓጉል ድረስ አያውቁምና አያዩም አሉ። በአጠገባቸውም የተቀመጡት አይሁድ መጥተው። ከስፍራው ሁሉ ይመጡብናል ብለው አሥር ጊዜ ነገሩን። ከቅጥሩም በስተ ኋላ በኩል ባለው በታችኛው ስፍራ ሰይፋቸውን ጦራቸውንም ቀስታቸውንም አስይዤ ሕዝቡን በየወገናቸው አቆምኋቸው። አይቼም ተነሣሁ፥ ታላላቆቹንና ሹማምቱንም የቀሩትንም ሕዝብ። አትፍሩአቸው ታላቁንና የተፈራውን ጌታ አስቡ፥ ስለ ወንድሞቻችሁም ስለ ወንዶችና ስለ ሴቶች ልጆቻችሁም ስለ ሚስቶቻችሁም ስለ ቤቶቻችሁም ተዋጉ አልኋቸው።ጠላቶቻችንም ይህ ነገር እንደ ደረሰልን፥ እግዚአብሔርም ምክራቸውን ከንቱ እንዳደረገው ሰሙ እኛም ሁላችን ወደ ቅጥሩ እያንዳንዳችን ወደ ሥራችን ተመለስን። ከዚያም ቀን ጀምሮ እኩሌቶቹ ብላቴኖቼ ሥራ ይሠሩ ነበር፥ እኩሌቶቹም ጋሻና ጦር ቀስትና ጥሩርም ይዘው ነበር አለቆቹም ከይሁዳ ቤት ሁሉ በኋላ ይቆሙ ነበር። ቅጥሩንም የሚሠሩትና ተሸካሚዎቹ በአንድ እጃቸው ይሠሩ ነበር፥ በአንድ እጃቸውም የጦር መሣሪያቸውን ይይዙ ነበር። አናጢዎቹም ሁሉ እያንዳንዱ ሰይፉን በወገቡ ታጥቆ ይሠራ ነበር ቀንደ መለከትም የሚነፋ በአጠገቤ ነበረ። ታላላቆቹንና ሹማምቱን የቀሩትንም ሕዝብ። ሥራው ታላቅና ሰፊ ነው፥ እኛም በቅጥሩ ላይ ተበታትነናል፥ አንዱም ከሁለተኛው ርቆአል የቀንደ መለከቱን ድምፅ ወደምትሰሙበት ስፍራ ወደዚያ ወደ እኛ ተሰብሰቡ አምላካችን ስለ እኛ ይዋጋል አልኋቸው። ሥራውንም ሠራን ከማለዳ ወገግታም ጀምሮ ከዋክብት እስኪወጡ ድረስ እኩሌቶቹ ጦር ይይዙ ነበር። ደግሞም በዚያ ጊዜ ሕዝቡን፦ ሁላችሁ ከብላቴኖቻችሁ ጋር በኢየሩሳሌም ውስጥ እደሩ በሌሊትም ጠባቂዎች ሁኑልን፥ በቀንም ሥሩ አልኋቸው። እኔና ወንድሞቼም ብላቴኖቼም በኋላዬም የነበሩት ጠባቂዎች ልብሳችንን አናወልቅም ነበር።›› ።

# ይቆየን፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org